**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት**
**The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order**
www.ethiopianorthodox.org

# ሰዓታት

ሰዓታት በሀገራችን ተጀመረ የሚባለው ባ15ኛዉ ክፍለ ዘመን በአባ ጊዮርጊስ ነው። ሰዓታት በጐላ የታወቀው የሌሊት ጸሎት እንደሆነ ነው፤ ነገር ግን ከሁለት በመከፈል የመዓልትና የሌሊት ሰዓታት በመባል ይታወቃል። የሰዓታት ቀጥታ ትርጉም በየሰዓቱ የሚጸለይ ሰዓቶችን ተመልክቶ የሚደርስ ጸሎት እንደነበር ክፍሉ ራሱ ያመለክታል። ይኸም ዓይነት ጸሎት ከነስሙ በግሪክ ኦርቶዶክስና በአንግሊካን በሌሎችም እንዲሁ ይገኛል፤ ስሙንም «ኦሬስ፣ አዎርስ» ይበሉት እንጂ ትርጉሙ ሰዓታት ማለት ነው። በሀገራችን ሰዓታት የሚደረሰው በሌሊት ሲሆን በብዙ ገዳማትና አድባራት በዓቢይ ጾምና፣ በፍልሰታ እንዲሁም በጥቂት ገዳማትና አድባራት ግን ከዓመት እስከ ዓመት ሳይቋረጥ ይቆማል።

ሰዓታት ጥንታዊ ጸሎት ሆኖ ሳለ በእኛ እስከ አባ ጊዮርጊሰ ዘመን ድረስ ቆየ ለማለት ያስቸግራል ምክኒያቱም ከሌሎች ሀገሮች በፊት ገዳማት በእኛ ሀገር ተስፋፍተዉ ተቋቁመው ስለነበር ነው። ባይሆን አባ ጊዮርጊሰ በማሳጠር፣ በመጠቅለል ወይም በማስረዘም አሻሻሉት ፤ ወይም የጥንቱን ትተዉ ራሳቸዉ ደርሰው አቅርበው እንደሆን አልተለየም፤ ይህ ገና ሰፊ ጥናት የሚጠይቅ ነው።  ምናልባት የጥንቱ ሌላ ሆኖ ይህ የአባ ጊዮርጊሰ ይሆንን? ወይስ ይህ የጥንቱ ሆኖ የአባ ጊዮርጊሰ ድርሰት ሌላ ይሆን? ይህ ሁለቱ አሻሚ ጉዳይ ነው። ምክኒያቱም ሰዓታት ተብሎ በስማቸው ከተጠራዉ ከገዳማቸው የተገኘዉ ሰዓታት አሁን ከሚደረሰው ሰዓታት ብዙ ለየት ያለ ነው። ምናልባት አባ ጊዮርጊሰ የደረሰው ይህ ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት አለ። ይኸውም የመጀመሪያ ቅጂ መጽሐፍ በመንበረ ጸባዖት ገዳም ይገኛል።

# የሰዓታቱ ክፍል

የሌሊት ሰዓታት ክፍል 3 ነው። ይኸውም 1ኛ/ አአትብ ወእትነሣእ 2ኛ/ ሚካኤል ሊቀ መላእክት 3ኛ/ ለኖኅ ሐመሩ ነው። ዜማው ግዕዝ፣ ዕዝልና አራራይ  የተቀላቀለበት ይሁን እንጂ ብዙው አራራይ ነው። በየክፍሉ ስለ ጌታችን፣ ስለ እመቤታችን በሰፊው ሲገልጽ ስለ ቅዱሳንም እንዲሁም አማላጅነታቸውን በመግለጥ ይናገራል። ድርሰቱም በግጥም መልክ የተዘጋጀ ነው። ከአአትብ ጀምሮ እስከ ሚካኤል ሊቀ መላእክት መጨረሻ ድረስ ያለው ብቻ የአባ ጊዮርጊሰ ድርሰት እንደሆን ሲነገር፤ ከኖኅ ሐመሩ ከሚለው ጀምሮ ያለው በየጊዜው በሌሎች የተደረሰ ነው።

ለኖኅ ሐመሩን ፣የእመቤታችንን ስብሐተ ፍቁር፣ ተፈሥሒ ማርያምን፣ ለአዳም ፋሲካሁ፣ ኦርኅርኅተ ሕሊናን የተባለው ዐፄ ልብነ ድንግል እንደደረሱት ይነገራል። የቅዱሳን ፣ የመላእክት ስብሐተ ፍቁር በየጊዜዉ እየተደረሰ የተጨመረ ነው። ከዚያ በኋላ ኪዳን ይደርሳል። ከመጀመሪያ አንስቶ እስከ መጨረሻዉ በየምዕራፉ እየገባ መስተብቁ ይጸለያል። ከዚህም ጋር ሰዓሉ ለነ....... እያለ ከሚሄደዉ ላይ በየጊዜዉ ተጨምሯል ምክኒያቱም ይህ ክፍል ከቦታ ቦታ ይለያያልና።

እንግዲህ ይህ መንፈስን ማራኪ የሆነ ድርሰት ከ6 ክፍለ ዘመናት በላይ አስቆጥሯል ማለት ነው።

(ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፤ ሊቀ ሥልጣናት ሀ/ማርያም  ከሳተሙት ባጭሩ የተወሰደ።)